# መንበርከክ ለምን?

ቤዛ/ከአዲስ አበባ/

አራተኛው አገራዊ ምርጫ ከአለፉት ምርጫዎች ጋር ሲነፃፀር የዴሞክራሲ ሂደት የጐለበተበት የሕዝቡ የፖለቲካ ብስለት የተንፀባረቀበት በመሆኑ ሰላም ወዳዶችን አስፈንድቋል፡፡ ነፃና ፍትሀዊው ምርጫ ያላስደሰታቸው ወገኖች ግን ገና ምርጫው ሰይጠናቀቅ የምርጫውን ዴሞክራሲያዊነትና ተዓማኒነት ለማጣጣል አሉባልታ መንዛትና መሠረተ ቢስ ክሶችን ማሰማት ጀመሩ፡፡ የ1997ን ምርጫ ያስተዋለው ሕዝብም ‹‹እረፉ! ሰላም ሰፍኖ ልማትን ማፋጠን እንሻለን››አላቸው፡፡ አንዳንድ ተቃዋሚዎች ከምርጫው በፊት፣ በምርጫው ዕለትም ሆነ ከዚያ በኋላ ‹‹ማስፈራራት ደርሶብናል›› የሚል መሠረተቢስ ውንጀላን ከማስተጋባት ጀምሮ የተለያዩ መሰናክሎችን ለመፍጠር እንቅስቃሴ ማድረጋቸው አልቀረም፡፡

በምርጫው ዕለት የመድረክ ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች ሰዓቱን ጠብቀው መገኘት ሲገባቸው ምርጫው ከተጀመረ በኋላ በመግባት ‹‹እኛ ባልተገኘንበት ምርጫው በመጀመሩ እንደገና ልናየው ይገባል›› በማለት የምርጫውን ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ጥላሸት ለመቀባት ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም፡፡ መድረክ ታዛቢዎቹን በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ማሰማራት ቢገባውም ‹‹የምርጫ ጣቢያዎች በመብዛታቸው ታዛቢዎቻችንን ማስቀመጥ አልቻልንም›› በማለት ምክንያት ሲፈጥር ተስተውሏል፡፡ የመድረክ ከፍተኛ አመራር ኋላ በተናጋሩት ሊያፍሩበትና ይቅርታ ሊጠይቁበት ምርጫው ተጀምሮ ዕለቱ ሳይጋመስ ‹‹ምርጫው ነፃ፣ ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ ያለመሆኑ ተረጋግጧል››የሚል መግለጫ መስጠታቸው ሂደቱን በነፃ ህሊና የሚከታተለውን ሁሉ አሳዝኖአል፡፡

የተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሁልጊዜም የኢትዮጵያ በጐ ነገሮች የማይዋጥለት የሂውማን ራይትስ ዎች የተቃውሞ ስልት የአንድ ሣንቲም ሁለት ገፅታዎች መሆናቸውን ሁለቱም የሰጡት መግለጫ ያመለክታል፡፡ ለሰው ልጆች መብት ተቆርቋሪ ነኝ

የሚለው የሂውማን ራይትስ ዎችም የመድረክ ከፍተኛ አመራር ከሰጡት መግለጫ ጋር ተመሳሳይነት ያለው መግለጫ ሰጥቷል፡፡ ምርጫውን ለመታዘብ በሥፍራው የተገኙ የሀገር ውስጥና የውጭ ታዛቢዎች መግለጫ ከመስጠታቸው በፊት ‹‹የኢትዮጵያ መንግሥት መራጮችን አስፈራርቷል፣ አስገድዷል፣ተፅዕኖም አሳርፎባቸዋል››ሲል በምርጫው ማግስት መንግሥትን ከመኰነኑም በላይ ምርጫው ተቀባይነት እንደሌለው አስታውቋል፡፡ የሁለቱም መግለጫዎች የሕዝብን አቋም በማስቀየር ላይ ያነጣጠሩ ቢሆኑም ወቅታቸውን ያልጠበቁና ተአማኒነት የሌላቸው በመሆናቸው የሕዝብ ጆሮ አላገኙም፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎችን መሠረተ ቢስ ተቃውሞ በማባባስ እንደፈለጋቸው የሚያሽከረክሩት መንግሥት የመመስረት ዓላማቸውና ፍላጐታቸው ያልተሳካላቸው ሂውማን ራይትስ ዎችና መሰሎቹ የሚያስተጋቡት ጩኸት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን አላገኘም፡፡

የሚበጀውን የሚያውቀውና በሳል፣ ብልህና ኩሩ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስተዳድረኛል ያለውን ፓርቲ መርጧል፡፡ በመላ ሀገሪቱ ‹‹ድምፄ ይከበር፣ በውጭ ኃይሎች ታዝሎ ሥልጣን መያዝ አይቻልም›› የሚሉና ሌሎችንም መፈክሮች በማንገብ በወጣው ሰልፍ አደባባዮችን አጥለቅልቋል፡፡ እናውቅልሀለን ያሉትን እነ ሂውማን ራይትስ ዎች እና መሰሎቹ አርፈው እንዲቀመጡና በኢትዮጵያ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገቡ የእፍረትን ሸማ የሚያከናንብ መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡

በጀግኖች ልጆቹ መስዋዕትነት መሪዎቹን የመምረጥ የዴሞክራሲ መብትን የተጐፀፈው የኢትዮጵያ ህዝብ የጭቆናው ሥርዓት ከተወገደለት ወዲህ የልማት ትሩፋትን አጣጥሟል፡፡ በዴሞክራሲ ሥርዓት ፋና ወጊነት የእድገት ብርሀን መፈንጠቁን በመገንዘቡ ይበጀኛል ላለው ፓርቲ ድምፁን ሰጥቷል፡፡ የሕዝቡ ውሣኔ ያልተዋጠላቸው አንዳንድ ተቃዋሚዎች፣ ሂውማን ራይትስ ዎች እና መሰሎቹ በተለያየ መልኩ ምርጫውን ማጣጣል ቢዳዳቸውም የሕዝብ ይሁንታን አላገኙም፡፡

ከምርጫው ፍፃሜ በኋላም ቢሆን የህዝብን ሉአላዊ ድምፅ ማክበር ያልፈለጉት እነዚህ ወገኖች ‹‹የምዝገባው ሂደት አወዛጋቢ ነበር፣ የመገናኛ ብዙሀን አጠቃቀም ችግር ነበረበት፣ ምርጫው ተጭበርብሯል›› እና የመሳሰሉትን መሠረተ ቢስ ክሶችና ውንጀላዎችን በመደርደር እንዲሁም ከዚያ በባሰ የምርጫው ይደገም ጥያቄን በማቀንቀን ላይ ይገኛሉ፡፡ ህዝብ ‹‹ድምጼ ይከበር›› በማለት ያስተጋባውን ተቃውሞ ወደጐን በመተው አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎችም የምርጫው ይደገም ጥያቄን ማቅረባቸው ማንነታቸውን በግልፅ ያሳያል፡፡ ይህም ለሕዝብ ጥቅም ሳይሆን ለግል ጥቅማቸውና ከበስተጀርባቸው ሆነው ቹ! ለሚሏቸው የውጭ ኃይሎች የቆሙ፣ ለሀገር ልማትና እድገት የማያስቡ እና ለሥልጣን የቋመጡ መሆናቸውን አሳይቷል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት  አራተኛውን የሕዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶችን ምርጫ ለማካሄድ የተቻለውን ሁሉ አድርጓል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ለምርጫ ቅስቀሳ የገንዘብ ድጐማ አድርጓል፡፡ ለምርጫ ፉክክሩ 43 ሚሊዮን ብር የሚገመት 550 ነፃ የአየር ሰዓት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ፈቅዷል፡፡ ይህም ሆኖ ግን ተቃዋሚዎች በራሳቸው ምክንያት የተሰጣቸውን ዕድል በአግባቡ አልተጠቀሙበትም፡፡ ምርጫውን ለማሳካት በርካታ የሰው ኃይል መሳተፉንና በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ወጪ መደረጉን በውል የሚያውቁት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለዚህ ታላቅ አገራዊ ጉዳይ የወጣው ወጪ ደንታ ሳይሰጣቸው ምርጫው እንዲደገም መጠየቃቸው ለአገርና ለህዝብ ተቆርቋሪ ያለመሆናቸውን ያመለክታል፡፡

ከዘጠና በመቶ በላይ ሕዝብ ድምፅ የሰጠበት ምርጫ ነፃ ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ እንደነበር የሀገር ውስጥና የውጭ ታዛቢዎች መስክረውለታል፡፡ በመላ ሀገሪቱ ከ40 ሺ በላይ ቋሚና ተንቀሳቅሽ የምርጫ ታዛቢዎችን ያሰማራው የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ጥምረት ምርጫው በሁሉም መለኪያዎች ሲመዘን ደረጃውን የጠበቀ፣ ፍትሀዊ፣ አሳታፊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ እንደነበር መስክሯል፡፡ የአፍሪካ ኅብረት ታዛቢ ቡድንም በተመሳሳይ መልኩ ምርጫው ነፃ፣ ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ መሆኑን አብስሯል፡፡ አገም ጠቀም ዓይነት ትዝብቱን ያሰፈረው የአውሮፓ ኅብረት ታዛቢ ቡድን ሳይቀር ኢትዮጵያ የተዋጣለት ምርጫ ማካሄድ የሚያስችል የምርጫ ህግ እንዳላት፣ ምርጫ ቦርድ ብቃት ያለውና በሙያው የተካነ መሆኑን፣ ለፓርቲዎች በቂ

የአየር ጊዜ መስጠቱን፣ በድምፅ ቆጠራ ሂደት ችግር ያለማጋጠሙን በአጠቃላይ ምርጫው ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ እንደነበር ገልጿል፡፡

ይህም ሆኖ የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ ቡድን የአሜሪካ ሬዲዮ ጣቢያ የአማርኛው ክፍለ ጊዜ(VOA) እንዳይደመጥ መደረጉ መራጮች ከተለያዩ ምንጮች ማግኘት የሚገባቸውን መረጃ ገቶታል በማለት መኰነኑ ድብቅ አጀንዳውን የሚያጋልጥ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ በቂ መረጃን ማግኘት የሚችለው ሀቅን መሠረት ካደረጉ የመገናኛ ብዙሀን ከመሆኑም በላይ ማንን መምረጥ እንደሚገባው ጠንቅቆ የሚያውቅ በሳል ህዝብ ነው፡፡ የአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን መሠረተ ቢስ ውንጀላ የሚያራግቡ፣ የአሻንጉሊት መንግሥት በመመሥረት የፖለቲካ ዓላማቸውን ማራመድ የሚፈልጉ የውጭ ኃይሎችን አስተሳሰብ ለማስረፅ የሚሹ መገናኛ ብዙሃን ውትወታና ጉትጎታ የኢትዮጵያን ህዝብ አቅም ማስለወጥ እንደማይችሉ የአውሮፓ ኅብረት ታዛቢ ቡድን ቢገነዘብ ኖሮ ይህን መሰል አፍራሽ ትዝብቱን ባላስቀመጠ ነበር፡፡

አውቀውም ይሁን ባለማወቅ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በምርጫው ቅስቀሳ ሰሞን የመንግሥት የመገናኛ ብዙሀን ለገዢው ፓርቲ ላደላ ፕሮግራምና ዜና ሽፋን ይሰጣሉ የሚል ወቀሳን ሲሰነዝሩ ቆይተዋል፡፡ ዛሬም የአውሮፓ ኅብረት ታዛቢ ቡድን የመንግሥት የመገናኛ ብዙሀን የዜና ሽፋን ለገዢው ፓርቲ ያደላ መሆኑን ተናግሯል፡፡

ሁለቱም ወገኖች የመንግሥት የመገናኛ ብዙሀን የመንግሥት ልሣን እንደመሆናቸው መጠን በሀገሪቱ የሚከናወኑ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ርዕሰ ጉዳዮችን በመዳሰሱ መረጃዎችን ለሕዝብ ማድረስ እንደሚኖርባቸው ሳይገነዘቡት ቀርተው አይመስለኝም፡፡ እውነታውን በመካድና የመንግሥት የመገናኛ ብዙሀንን የገዢው ፓርቲ ልሣን በማስመሰል ለማደናገርና ወደ አንድ ወገን ያደላ ሥራ የሰሩ ለማስመሰል መሞከራቸው ትዝብት ላይ ሳይጥላቸው አይቀርም፡፡

ምንም ይሁን ምን የኢትዮጵያ ሕዝብ በተረጋጋ መንፈስ፣ በሰላማዊ መንገድ፣ በነፃነት፣ ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ አካሄድ፣ ጨዋነት በተላበሰ መልኩ ትክክለኛ ፖሊሲና ስትራቴጂ ላለው እና ከድህነት አዘቅት ያወጣኛል ላለው ፓርቲ ድምፁን ሰጥቷል፡፡ ድምፁ እንዲከበርለትም በአደባባይ ሰልፍ ጠይቋል፡፡ ድሉን ለተጐናፀፈው ፓርቲም አጨብጭቧል፡፡ የተጀመረውን ልማት ማስቀጠል የሚችለው ኢህአዴግ ብቻ መሆኑን መስክሯል፡፡ የተሸነፉ ፓርቲዎችም ከአሸናፊው ፓርቲ ጋር በመተባበር ለልማት እንዲሰሩ ጥሪ አድርጓል፡፡ ከዚህ ውጭ ሰላሙን የሚያደፈርሱ፣ ልማቱን የሚያደናቅፉ ኃይሎች ቦታ እንደማይኖራቸው አሳስቧል፡፡

ህዝቡ ድምፁ እንዲከበርና የውጭ ኃይሎች ከኢትዮጵያ ላይ እጃቸውን እንዲያነሱ ባደረገው የተቃውሞ ሰልፍ ላይ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ባሰሙት ንግግር መንግሥት ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር በመተባበርና ሀሳብን በመጋራት ለልማት እንደሚሰራ ገልፀዋል፡፡ ይህ ንግግራቸውም ህዝቡን እልል አሰኝቷል፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሥልጣን ጥማታቸውን ለማርካትና ለወንበር ከመሽቀዳደም ይልቅ ለህዝብ ጥቅምና ለሀገር እድገት ቅድሚያ ቢሰጡ ከበሬታን ያስገኝላቸዋል፡፡ የውጭ ኃይሎች ግፊትን መከታ በማድረግ የህዝብን ሉአላዊነት ለመርገጥ ማሰብ ተፎካካሪነታቸውን ከማደብዘዙ በስተቀር በተያዘው የልማት ርብርብ ላይ ቅንጣት ታክል ገንቢም ሆነ አፍራሽ ተፅዕኖ አያሳድርም፡፡

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ሰልፍ ለወጣው ህዝብ ባደረጉት ንግግር ‹‹ይኼ ህዝብ ክብሩን ጠብቆ መራብ የሚያውቅ ህዝብ ነው›› ብለዋል፡፡ በእርግጥም የኢትዮጵያ ህዝብ ክብሩን በጥቅም የማይለውጥ ኩሩና ሉዓላዊነቱን የማያስደፍር ህዝብ መሆኑን ዓለም መስክሮለታል፡፡ ጥንትም ዳር ድንበሩን በመድፈር የቅኝ ተገዢ ሊያደርጉት የሞከሩ የውጭ ኃይሎችን በማንበርከክ የነፃነት ተምሳሌትነቱ በዓለም እንዲናኝ አድርጓል፡፡

ዛሬም ቢሆን የተቃዋሚ ፓርቲዎች ደጀን በመሆን ስንዴን እያሳዩ እንዳሻቸው የሚጠመዝዙትን መንግሥት ለመመሥረት የሚፍጨረጨሩ የውጭ ኃይሎችን እንቢ አሻፈረኝ ማለቱ አልቀረም፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ እፎይታን አግኝቷል፡፡ በሰላም ወጥቶ ይገባል፡፡ ለልማት ዘብ የቆመ፣ ድህነትን ታሪክ የሚያደርግ ፖሊሲና ስትራቴጂ ያለው መንግሥት አግኝቷል፡፡ ከእንግዲህ ወዲያ ሁከትና ብጥብጥን በመፍጠር የውጭ ኃይሎች መሣሪያ የሚሆኑ ወገኖችን ማስተናገድ አይፈልግም፡፡ ፊቱን ወደ ልማት በማዞር በስንዴ ሊደልሉት የሚፈልጉትን ማሳፈርና ሠራተኛ ህዝብ መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ ይፈልጋል፡፡ ህዝቡ የጀመረውን ልማት መቀጠልና በአጭር ጊዜ ውስጥ ድህነትን ታሪክ ማድረጉ የማይቀር መሆኑን ጅምሩ ይመሰክራል፡፡

አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ከተጠናወታቸው የአሉባልታና የእድገት አደናቃፊነት አባዜ ተላቅቀው ለሀገራቸው ልማትና እድገት መቆርቆርና መሥራት፣ ለህዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ይሁንታ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተፎካካሪነታቸውም መሠረት ማድረግ የሚኖርባቸው እነዚህኑ ሀቆች ይመስለኛል፡፡ አስተምራና ተንከባክባ ተወዳድረን ህዝብን እንምራ ለማለት ያበቃቻቸው እናት ኢትዮጵያ በመሆኗ ህሊናቸውን ለውጭ ኃይሎች መሸጥ አይኖርባቸውም፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ መንግሥት የውጭ ኃይሎች ለሚያሳድሩት ተገቢ ያልሆነ ተፅዕኖና መሰረተ ቢስ ውትወታ የማይንበረከኩ መሆናቸውን ተገንዝበው አቋማቸውን ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተቃዋሚዎች፣ የውጭ ኃይሎች የሚጐትቷቸው ጋሪዎች ከመሆን ይልቅ የልማት ፊታውራሪ በመሆን የህዝቡን ተአማኒነት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ሞግዚት የማይሹ በራሳቸው የሚተማመኑ ቆራጥ የኢትዮጵያ ልጆች መሆናቸውን በተግባር ማሳየት ይበጃቸዋል፡፡ ሽንፈታቸውን ተቀብለው ከአሸናፊው ፓርቲ ጋር መሥራት ክብርና ሞገስን ያጐናፅፋቸዋል፡፡

በቀጣይ የሚፈጠሩ ዴሞክራሲያዊ መድረኮችንና መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሰላም፣ በፍቅርና በመቻቻል ከአሸናፊው ፓርቲ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው ለመሥራት ራሳቸውን ያዘጋጁ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝቦች መንበርከክ ለምን? በሚል ከድህነት ለመውጣት የሚደረገውን ትግል በማፋፋምና ልማትን በማፋጠን ባለሁለት አሀዝ ዕድገት ያስመዘገቡበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ በዚህም ለማንም እና ለምንም ፀረ እድገትና ልማት ኃይሎች የማይንበረከኩ መሆናቸውን አስመስክረዋል፡፡ ለሁሉም አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ሆኑ የውጭ ኃይሎች ፊጦ የሚታየውን ሀቅ ዐይኔን ግንባር ያድርገው ብሎ ከመካድ ቆም ብለው ራሳቸውን ይመርምሩ እላለሁ፡፡